የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

**የካቲት| 22/2002**

## <u>ደብዛቸው ስለጠፉ እስረኞች ጥየቃችን አያቋርጥ</u>

**የሕዝብን መብት ባለማቋረጥ እየረገጠ ያለው የወያኔ ቡድን ለስልጣን ከበቃ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ዜጎችን አስሮ ደብዛቸውን እንዳጠፋ የሚታወቅ ነው:: አልያዝኳቸውም ብሎ ከመካድ ጀምሮ እስከ ምንም ገለፃ አለመስጠትን ፖሊሲው ወይ አቅዋሙ ያደረገው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በዚሁ ደብዛ የማጥፋት እርምጃው የዜጎችን መሰረታዊ መብት በዕብሪት መርገጡ ተጋልጧል::**

**ደብዛቸው ከጠፉ እስረኞች መሀል የኢሕአፓ አመራር ኮሚቴና የከፍተኛ እርከኖች አባላት የነበሩ በርካታዎችን መጥቀስ እንችላለን:: ከጎንደርና ጎጃም በ1983 የተያዙትን እን ፀጋየ ገብረ መድህንና ጓዶቹን፤ ከአዲስአበባ የተያዙትን እነ አበራሽ ለማና ጓዶቿን፤ ጋዜጠኛ ብርሀኑ እጅጉን፤ ከባሕር ዳር የተያዙትን እነ አበበ አይነኩሉን፤ ወንዱ ሲራክ ደስታን፤እነ ደምሴን ከአርባ ምንጭ ወዘተ በተመለከተ የወያኔ መሪዎችአልሰማንም አላየንምን መርጠው ቆይተዋል:: ዛሬ ከመለስ ዜናዊ ጋር ተጋጭተን ተቃዋ ሚ ሆነናል የሚሉት ግን ትላንት ለነፀጋዬና አበራሽ ሁሉ ደብዛ መጥፋት እርምጃ ዋና ተጠያቂ የነበሩ ት እነ (አቶዎች) ስዬ አብርሀ ፤ገብሩ አሥራት፤ ተወልደና አለምሰገድም ቢሆኑ ምንም አናውቅም ማለትን መርጠዋል::ዛሬ ለኢየሱስ አደርኩ የሚለውና ትላንት ግን በነፀጋዬ ላይ ከወሰኑት አንዱ የነበረ ውም ታምራት ላይኔ ንስሐ ገባሁ ያለው ስለዚሁ ጉዳይ መናገርን የሚጠቀልል ሆኖ አልተገኘም:: የወያ ኔ አገዛዝ ደብዛቸው ስለጠፉው የፖለቲካ እስረኞች እንዳይጠየቅ ብዙ ጥረትን እያደረገ ሲሆን አንዱ ዘዴው ተገድለዋልና ጊዜ አታጥፉ የሚል መሆኑም ታውቋል:: በዚሁ ዜናውን የማፈን ተልዕኮው ደግሞ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ነን ባይ ተቋሞች(አምኔሰቲ፤ህዩማን ራይትስ ዋች) ና የሀገር ቤቱ ኢሰመጉም ቢሆኑ በተጨባጭ ተባባሪ በመሆን ዝምታን አቅፈዋል:: ስለነ ፀጋዬና አበራሽ ጥያቄ አያሰሙም--ስለነዚህ ቀርቶ በግፍ ስለታሰረው አቶ አበራ የማነአብም ተቃውሞ አያሰሙም::**

**ሰሞኑን አንድ ከወያኔ የውስጥ ዜና ምንጮች ጋር ግንኙነት አለኝ የሚል ግለሰብ ከስድስት ወር በፊት አንድ ውስጠ አዋቂ እነ ፀጋዬ ገብረ መድህን መገደላቸውን ነግሮኛል፤ ማን እንደገደላቸውና**

እንዳስገደላቸውም አውቃለሁ ያለ ሲሆን ቃለ መጠይቅ አቅራቢዎቹ ግን እነማን ብለው እንኳን ሳይጠ ይቁ እንዳሰናበቱት ሰምተናል፡፡ ግለሰቡም አሁንም ቢሆን አውቃለሁ የሚለውን ለሕዝብ እንዲያሳውቅ መጠየቅ ያለበት ሲሆን ኢፖእአኮ ግን ደብዛቸውን ያጠፋው የወያኔ አገዛዝ በይፋና በህግ ፊት የት እንዳደረሳቸው እስከሚያምን ድረስ ደብዛቸው ለጠፉ እስረኞች መጮኻችን መቀጠል አለበት ብሎ ለዜ ጎች ሁሉ ያሳስባል፡፡ ደብዛ በማጥፋቱና ይህንንም በመደበቁ የተሳተፉ ሁሉ በወንጀሉ ተጠያቂ መሆናቸ ውም ግልፅ ነው፡፡ተገድለዋል በሚል ዝምታ ግን ለወያኔ አገዛዝ የሚያመችና ወንጀሉንም የሚያረሳሳለ ት ይሆናል፡፡ ስለዚህ በወያኔ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚነዛውን አደናጋሪ “ ዜና” ወደ ጎን ትተን ደብዛቸው የጠፋው ሁሉ የት ደረሱ ጥያቄያችንን እንቀጥል፤ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ እንዲፈቱ ትግላችንን እናፋፍም፡፡

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM

**WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE**